# ወቅታዊ ጥሪ

የወያኔን አስቂኝ ምርጫ ተከትሎ በኢሕአፓ ለሀገር ወዳድ ሀይሎች የተላላፈው ጥሪ ወቅታዊ መሆኑ በልዩ ልዩ አቅጣጫዎች ተስተጋብቷል። ጥሪው የሚመለከተው የወያኔ አገዛዝ የሕዝብ ጠላት ነው ብለው የሚያምኑና ሁለገብ ትግልን ለማካሄድ ለተነሱ ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ግልፅ ነው።

ከዚህ ቀደም ሰላማዊ ትግልና ሁለገብ ትግልን አቃርነው በማቅረብ ውዥንብር ሲነዙ የቆዩትን የምናውቃቸው ቢሆንም በተለይ ከ1997 ወዲህ ደግሞ የወያኔን አገዛዝ በሰላማዊ መንገድ ወይም በምርጫ መጣል እንደማይቻል በሚገባ ተረጋግጧል። ያለፈው ሰሞን የምርጫ ቧልትና የወያኔ ፍፁም አሸናፊነት ይህንኑ በባሰና በአስከፊ መልኩ አሳይቷል። የወያኔ አገዛዝ ከዴሞክራሲና ከተራ ይሉኝታ ጋር የተቆራረጠ ፀረ ሕዝብ አገዛዝ ነውና በአምባገነንነቱ ሊቀጥል ወስኗል። ወያኔ ስለ ራሱ ማንነት ምንም ብዠታ የለውም--ለዚህም ነው መለስ ዜናዊ ደጋፊ ብሎ ለሰልፍ ከጠራው ሕዝብ ሳይቀር በመስተዋት ሳጥን ገብቶ የሚደበቀው። ወያኔ ተቃዋሚ የተባሉትን ድርጅቶችና አመራሮችም በሚገባ ያውቃል፤ጠንካራና ደካማ ጎናቸውንም አጥንቶ ሊከፋፍላቸውና ሊያዳክማቸው ችሏል። ብዙ ሚሊዮን ብር አውጥቶም ቅጥረኞቹንና ሰርጎገቦቹንም በውጭ ሀገርም ሳይቀር አሰማርቷል። በአንፃሩ ግን ተቃዋሚ ሀይሎች የወያኔን አገዛዝ መሰረታዊ ጠባይ፤ ድክመትና ጥንካሬ በተመለከተ ተገቢውና ትክክለኛ ግንዛቤ ነበራቸው/አላቸው ማለት ያስቸግራል።በመሆኑም ወያኔ ብዙ ጊዜ ሊያደናግራቸውና ሰለባው ሊያደርጋቸው ችሏል። በ1997ም ታይቷል፤ በአሁኑም ምርጫ ተብዬ ቧልት እንደገና ታይቷል። ለነገሩ ገና በ1983ም ታይቶ ነበር ቢባል ስህተት አይደለም።

ተቃዋሚ ድርጅቶች ዛሬም ቢሆን ውስጣቸውን በጥሞናና በድፍረት በመመርመር የተሳሳቱትን ለማረምና ድክመታቸውንም ለማስወገድ መነሳት እንዳለባቸው ግልፅ ነው። የኢሕአፓ ወቅታዊ ጥሪ የወያኔን አገዛዝ ይዘትና ጠባይ መሰረት ያደረገ ነው። ወያኔን በኤኮኖሚው መክክ መታገል፤ በምርጫ ገብቶ ቀስ በቀስ ማዳከም፤በሰላም ለወጥን መጠበቅ የሚሉት አቅዋሞችና አማራጮች ሁሉ ሀገርን ጎጂና የወያኔን ዕድሜ የሚያራዝሙ ናቸው ከሚለው ድምዳሜ የተነሳ ነው። ለዚህም ነው ከዚህ ዓይነቱ አቅዋም ርቀውና ሁለገብ ትግልን መርጠው በዚህ መንገድ ለሚታገሉና ሊታገሉ ለሚጥሩት ጥሪው የተላከው። ድርጅቶችን ትላንት ሲከፋፍሉ ወይም ከወያኔ ጫማ ስር ሊወድቁ ሲለማመኑ የነበሩ አንዳንድ መሰሪ ክፍሎች ደግሞ ለሚቀጥለው ርኩስ ተልዕኮአቸው ያመች ዘንድ ፀረ ወያኔ ነን ብለው መጮህ ቢጀምሩም እነዚህን ከታጋዮችና ከሕዝብ ጎራ የሚያርቅ ጥሪም ነው። ፀረ ወያኔው ትግል በአስመሳዮችና የትግል ወኔ ከቶም በሌላቸው የስልጣን ጥመኞች መጨናነቅ የለበትም። የታጋይነት መለኪያው ወያኔን በሁሉገብ ትግል ለመጣል ቆርጦ መነሳትና ሞት አይፈሬነትን በተግባር ማስመሰከር እንጂ ራሰን ማዳነቅ ወይም ምርጥ ምሁር ነኝ ብሎ መኮፈስ መኩራራት ሊሆን አይችልም። ጥሪው ህልውናቸው ለተረጋጋጠ ድርጅቶች መሆኑም ካለፉት የግንባር ምስረታ ተመክሮዎች የተገኘ ትምህርትን የተመረኮዘ ነው። ከዚህ

ቀደም ኢሕአፓ እንደ ድርጅት በእኩል ድምፅ ከሌሎች ጋር በመጣመር ያደረገውን አስተዋፅዖ ሊክዱ የሚነሱ ባይጠፉም ሀቁ ግን ድርጅቱ ህልውናቸው አጠያያቂ ከሆኑ ቡድኖች ጋርም በእኩ ል ድምፅ በመያያዝ ሊታገል መሞከሩ ለህብረቶቹ ድክመት አንዱ ምክንያት ነው ተብሎ የተገመ ገመ ነው። ስለዚህም የትብብር መሰረት ህልውና ያላቸው ድርጅቶች ሆነው ሰፋ ያለውን ክፍል ደግሞ በዚሁ መሰረትና ምሰሶ ዙሪያ ማሰባሰቡ ሊቀጥልም የሚችል ነው።

መዋቅራዊ ግንባር ከሚለው በመለስ መወያየትና ትብብርን መፈለግ የሚለው ደግሞ ይህን የጋራ ስምሪት መስመር ማለትም ወሳኙ ትግል ሁለገብ መሆን እንዳለበትና የወያኔን አገዛዝም ጠላት ብሎ ፈርጆ ለመጣል መነሳት እንደሚገባ፣ የሕዝብ ጎራ መጠናከር እንዳለበት፣ ትግላችን ሀገር አድን መሆኑን፣ለዴሞክራሲና ለኢትዮጵያ መሆኑን በምልዓት ሕዝቡ ዘንድ ማስፋፋትና ሕዝብም በአንድነት በወያኔ ጠላትነት እንዲነሳ ማድረግ ማለት ነው። ወያኔ ዕድሜው የረዘመበት አንዱ ምክንያት ሕዝብን ሊከፋፍል በመቻሉ ነው። የሕዝብን ጥያቄ አንግበው በመታገል ታሪክ የፃፉት ወጣቶችና በተለይም የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች መሆናቸውን ወያኔ ያውቃልና ተማሪዎችን በብሄረሰብ ከፋፍሎ እያናከሰ ለሕዝብ ድምፅ እንዳይሆኑም ለማድረግ ችሏል። ሕዝብንም በክልል ሸንሽኖ አንዱን በሌላው ላይ አነሳስቶ በጋራ እንዳይነሳበት ለማድረግም ችሏል። ተለጣፊዎችን ኮልኩሎ፣ የትግራይን ሕዝብንም ለመነጠል ቀን ተሌት እየሰራ፣ በትምክህት እየተቃኘና ፍጅትን ም እያካሄደ ከርሟል። ይህን መቋቋምና ህዝብ የህብረትና የጋራ አቅዋምና ትግልን ጠቃሚነትና ወሳኝነት ተገንዘቦ ኢትዮጵያን ለማዳን በጋራ እንዲነሳ ለማድረግ መቻል አስፈላጊ ነው። ጥሪው በውስጥ ይህንም መልዕክት የያዘ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በአብዛኛው ስለወያኔ ማንነት የተዛባ ግንዛቤ የለውም። ሰለባ ያደረገው መከፋፈሉና በቂ ና ተገቢ ድርጅታዊ ቅርፅና አመራር የሚሰጠ ው በማጣቱ ነው። በወያኔ ስር ምርጫ ፋይዳ ቢስ መሆኑን በመገንዘቡ አልተመዘገበም። ብዙዎች ም የማዕቀብን ጥሪ ሰምተው አለመሳተፋቸው የሚደበቅ አልሆነም። ስለዚህም ሕዝብ ብዠታ ከሌለውና ወያኔንም ለማውደም ፍላጎት ካለው በጋራ እንዳይነሳ የሚያግደውን ጋሬጣ ሁሉ ማስወ ገድ ተገቢ ይሆናል። አንድነቱን የሚያደናቅፈውን ሁሉ ማስወገድ፣ ማሸነፍ ያስፈልጋል ማለት ነው።

ከዚህ ሌላ የሀገርና የሕዝብ ህልውና ጉዳይ ነውና ይህን ከባድና ወሳኝ ግዳጅ ለማንም አሳልፎ መስጠት የሚቻል አለመሆኑን ጥሪው ጫና ሰጥቶ ያቀርባል። ወያኔን ጠላት ብለው በሁለገብ ትግል ሊያስወግዱት ለተነሱ ሀገር ወዳዶች በሚል የቀረበውም ከዚህ የተነሳ ነው። ዶሮ አንዴ እንኳን እንዳይጮህ አንቀው በሩጫ የሚክዱ፣ በሕዝብ ላይ ወንጀል ፈፅመውና አጠፉን ማለቱ አቅቷቸው የሚገኙ፣ አገዛዙን ለማስወገድ ሳይሆን አድሰው ሊቀጥሉ የሚፈልጉ፣ ከአገዛዙ መሰረታ ዊ ልዩነትና ቅራኔ ከቶም የሌላቸው፥ ትግልን መምራት የማይችሉና ፖለቲካን ለግል ስም ማስጠ ሪያና መዝናኛም ዓይነት አድርገው የሚወስዱ፣ ከወዲሁ ሙስና የጠለፋቸው፣ ለትግል አስፈላጊ የሆነው ወኔ ያጠጠባቸው ወዘተ በፖለቲካው መድረክ ብቅ ብለው ያዙን ልቀቁን ሲሉ ሕዝብም

በዚህ መደናገር እንደሌለበት ጥሪው ይጠቁማል፡፡ ሀገራችንን ማዳን አለብንና ሀገርና ሊገዛ በርከ ት ያለ ገንዘብና ወታደር ይዞ ብቅ ላለው ሁሉ የሚደፉትን መሪ ማድረግ ስህተት ይሆናል፡፡ አጋር የምንላቸውም እውነትም ለኢትዮዕያ ወዳጅ ናቸው ወይስ ሀገራችንን ለመጉዳት ተጠቅመውብን ያሰወግዱናል የሚለውን ከወዲሁ በጥሞና መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ የጎረቤት፤ የአካባቢና የዓለ ም አቀፍ ሁኔታንም በማጤን በዚህ ደረጃ ወዳጅ ጠላትን፤ ዛሬና የነገውን መለየት መቻል ይገባና ል፡፡ እንወያይ፤ እንመካከር፤ተነጣጥለን መጠቀሚያ ከመሆን እንዳን የሚለው የጥሪው መልዕክት በዚህ መልክ ግልፅ ነው፡፡

ኢሕአፓ ይህን ወቅታዊ ጥሪ ያደረገው በጥሪው ግልፅ እንደሆነው ሁሉ የህብረት ግንባር በሚል መዋቅር ተቻኩሎ ለመግባት ሳይሆን የወያኔ አገዛዝ በሁለገብ ትግል ብቻ መውደቁ/ሊወድቅ መቻሉ ግልፅ ነውና ተባብረን ትግሉን እንያያዘው ለማለት ነው፡፡ አንዳንዶች ሲሉ እንደነበረው ለወያኔ ሌላ 15 ዓመት መስጠቱ ቀርቶ አንዲትም ዓመት መለገስ ኢትዮጵያን ወደ ባሰ ችግርና ቀውስ የሚከት ነውና ጊዜ የለንም፡፡ 19 ዓመት ብዙና ከብዙም በላይ ነው--ሕዝባችን ጠንካራ ሆኖ እንጂ ከህዲዎቹ እነ መለስ ሀገራችንን ድምጥማጧን ባጠፏት ነበር፡፡ ያለንበትን ሁኔታ በድፍ ረት ስንመረምረው የሕዝብ ጎራ ነን ያሉ ድርጅቶች ተከፋፍለውና ተዳክመው ይገኛሉ፡፡ ከ 1997 ኡ ሲወዳደር ይህ ችግርና ድክመት ተባብሶ ይገኛል እንጂ አልተቀረፈም፡፡ የከፋፋዮች፤ በጥባጮ ችና አንጃዎች መርዝ ሁሉንም ድርጅት አጥቅቶታል፡፡ የወያኔ ቀጥተኛና የእጅ አዙር ደጋፊ የሆኑ ባዕዳንም ድርጅቶችን በመከፋፈሉ መሰክ በትጋት ሲሰሩና ጉዳት ሲያደርሱ አይተናል፡፡ በመሆኑም ሀቂሮ ሀገር ወዳድ ድርጅቶች ራሳቸውን ለማጠናከር ትኩረት ሰጥተው መንቀሳቀሳቸ ው የሚደገፍ ቢሆንም ትብብር ሊደረግ ከተቻለ ደግሞ-- በአዲስ መሰረትና ግንዛቤ መሰረት ማለ ት ነው--ጠቀሜታው የሚያከራክር ሊሆን አይችልም፡፡ ለዚህም ነው ትኩረት ተሰጥቶት በጥንቃ ቄ መሞከር ያለበት፡፡ የዚህ ትብብር መሰረትና መነሻ ሊሆኑ የሚችሉትን መሰረታዊ ጉዳዮች ጥሪ ው የዘረዘረ ቢሆንም የኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ስር መደረግ ያለበት ጥረትና ትብብር መሆኑ ደግ ሞ ከቶም ሊያከራክር አይችልም፡፡ ላሉት አቢይ ችግሮች መፍትሄው መፈለግ ያለበት በኢትዮጵ ያ ዴሞክራሲያው አንድነት ጥላ ስር እንጂ ኢትዮጵያን ለመገነጣጠል በተቃኘ ግብ መሰረት ሊሆ ን አይችልም፡፡ ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ተብሎ በውጭ እጅና የሀገርን አንድነት በተፃረረ መንፈስ ተሞክሮ የነበረው ስብስብ በአስቸኳይ የተጨናገፈውና የከሸፈውም ሀገርን ጎጂ በመሆኑ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ጠላት ወያኔና በሀገርም በውጭም ያሉ ጭፍሮቹ ኢሕአፓ ጠላታችን ነው እያሉ ማጓራታቸው ድርጅቱን የሚያስደስተውና የሚያኮራው መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ እነዚህን አጋን ንቶች ካስጓራቸው ጥሩ ለመስራቱ ዓይነታ ምስክርነት ነውና፡፡ ጠላትን ወዳጅ ማለት ምን ያህል ጎጂ ለመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማጠየቂያ ደርድሩልኝ የሚለን አይሆንም፡፡ ጠላት ወዳጅ ላይሆ ን መልፈስፈሱ ይብቃ፤ ቅሌትና ውርደት፤ ተለጣፊነትና አንጃነት ያክትም ያለ ሕዝብ ነው፡፡

ወያኔ ዳግም ቢፈጠርም ፀረ ኢትዮጵያነቱ የሚለቀው አይደለም:: የወያኔን መርዝ የተጋቱ ሁሉ መድሀኒት ፈልገውና ተፈልጎላቸው በይፋና በሕዝብ ፊት ይህን ቡድንና ዘረኝነቱን አውግዘው ይገኙ፤ ስርየትንና ይቅርታን ይፈልጉ መባሉም አግባብ ያለው ነው:: ሌላው ሳንጠቅሰው የማናል ፈው ጉዳይ ደግሞ ዛሬ የሕዝብ ጎራ ተብሎ አጥር የለሽ ግቢ ገብተው ወንበር የያዙና መድረኩን የጨበጡ ብዙ ወንጀለኞች እንዳሉ ነው:: በደርግም በወያኔም ጊዜ ደም ያፈሰሱ፤ ሽብር ያካሄዱ፤ ስየል የፈፀሙ፤ ስንቱን ንፁህ ዜጋ የጨፈጨፉ:: በየድርጅቱና በየጉራንጉሩ ተሸጉጠው ታጋይ የሚለውን ካባ በቡትቶነት ለብሰው፤ታሪካቸውን ወንጀላቸውን እየካዱ፤ ታጋይ በሉን መሪ በሉን ብለው የትግሉን ሂደት የሚያደናቀፉ በርክተዋል:: ዋና ትኩረታችን በዋናው የወቅቱ ጠላታችን ይሁን ቢባልም አሳርፍ ያለች ጣት ዓይነት ደም ያሰከራቸው ሽብርተኞች፤ወንጀለኞችና ከሀዲዎ ች፤ ከደርግም ከወያኔም ጋር ሆነው ደም ያፈሰሱ አውሬዎች የሕዝብን ጎራ በማተራመስ ላይ አሉ:: ብንተዋቸውም እነሱ ሰለባቸውን አልተዉም--ዛሬም ሊያጠፉት ይወራጫሉ:: ይባስ ብለው ቀይ ሽብር መደረጉን ሳይቀር ሊክዱና የቀሰለውን ሕዝብ ዳግም ሊያደሙት ተነሰተዋል:: የተወሰ ኑት ሌላ ቢሉም በወያኔ የተገዙ ናቸውና ሞት ለኢሕአፓን መፈክራቸው ቢያደርጉ አስገራሚ ሊሆን አይችልም:: የሚጠበቅ ነው:: እነዚህን ተምቾች ከሕዝብ ጎራ መንጥቆ ማውጣትና ወደ ታሪክ ትቢያ አሊያም ወደ ወያኔ ጎራ መመለሱ በጣም አስፈላጊ ነው:: የሕዝብን ትግል እያቆሸ ሹና እያደናቀፉ ጉዳት ሲያደርሱ ዓመታት ቆጥረናልና::

ወቅታዊው ጥሪ ጎራችንን እናፅዳ ማለቱ አስፈላጊና ተገቢም ነው:: ጠንከርኩ ያለን ጠላት ለማሸነ ፍ በሀገር ወዳዶች ውስጥ ያለውን ድክመት ሳንሸፋፍን አውጠተን መርምረን ማስወገድ መቻል አለብን:: ይህ ቅንጦት ሳይሆን ግዳጅ ነው:: ስህተታችን ካወቅን አንደግመውም፤ ድክመታችንን ሳንደብቅ ይህ ነው ካልን ማስወገጃ መድሀኒት እንፈልግለታለን:: ደጋፊዎችም አሰመሳዩን ሳይሆን ሀቀኛውን የሕዝብ ታጋይ ለመደገፍ መነሳት አለባቸው--ፀሀይ ጨረቃ ይዣለሁ ላለ አፈጮሌና ሀሳዊ መሲህ ሁሉ ዕልልታና ገንዘብ ልገሳው መቆም አለበት:: አሞሌውን ራሳችን ካላከበርን መጫወቻ ብንሆንና ነጋ ጠባ ደግሞ ብስጭትና ድቀት ቢገጥመን መውቀስ ያለብን ራሳችንን ነው :: ደርግ ቡና ሊሸጥ ሲነሳ ከወሬው ቀነስ ከቡናው ቀነስ ሲለን እንደነበረው ከሞቅ ሞቁ መራቅ፤ሀገ ራችንን ማዳን እንዳለብን በሚገባ መገንዘብ፤ ከወያኔ ቅጥረኞችና ሎሌዎች መራቅ፤ ስለ ትግል ማውራቱን አቁመን ትግላችን በገቢር እንዲስተጋባ ማድረግ አለብን:: ሕዝብን ለናቁት ወያኔዎች ና ባዕዳን ጌቶቻቸው ትምህርት እንስጣቸው:: በዚህም መሰረት ኢሕአፓ ያቀረበው ጥሪ ወቅታዊ ና ሁሉም ሃቀኛ የኢትዮጵያ ልጆች ጆሮ ሊሰጡት የሚገባ ነው::

የወያኔን አገዛዝ በቆራጥ ትግል ለማውደምና ሀገራችንን ለማዳን እንነሳ !!